*መልእክት ሁለት*

## *ሰይጣናዊ ኃይላትን በማሸነፍ የከነዓንን ምድር የራስ ማድረግ*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1፡2፣ 6፣ 11፤ 5፡13-15፤ 6፡1*

**I. በብሉይ ኪዳን ምሳሌ፣ የምሳሌዎች ስብስብ አለ፣ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ በተመለከተ የዚያ ምሳሌ ሙሉ መፈጸም አለ—1 ቆሮ. 10፡3-4፣ 1፣ 11።**

**II. መጽሐፈ ኢያሱ ጥልቅ ምሳሌዎች ያሉት መጽሐፍ ነው—1፡13፤ 2፡18፤ 3፡3፣ 10-11፤ 5፡12፤ 6፡6።**

**III. የመጽሐፈ ኢያሱ ውስጠ-መሰረታዊ ትርጉም ምድሪቱን መውሰድ ነው—1፡2፣ 6፤ 5፡12።**

**IV. የእስራኤላውያንን ወደ ከነዓን መግባት እና በከነዓን የነበረውን ውጊያ ትርጉም ለመረዳት፣ ከነዓን በምሳሌ ሁለት እጥፍ ትርጉም እንዳላት ማወቅ ያስፈልገናል—ቆላ. 1፡12፤ ኤፌ. 1፡3፤ 2፡2፤ 6፡12፦**

*ሀ. በአዎንታዊ ጎኑ፣ የብልጥግናዎች ምድር የሆነችው ከነዓን ፍሊጋ የሌለው ብልጥግናዎች ያሉትን ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስን ታመለክታለች—ዘዳ. 8፡7-10፤ ቆላ. 1፡12፤ ኤፌ. 3፡8፦*

1. *መልካሚቱ ምድር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ ምሳሌዎች ከፍተኛው-ምርጡ-የመጨረው የክርስቶስ ምሳሌ ናት—ዘዳ. 8፡7።*
2. *መልካሚቱ ምድር፣ የከነዓን ምድር፣ ሁሉን እና በሁሉ ውስጥ የሆነውና ሁሉ ነገራችን የሆነው ክርስቶስ ምሳሌ ናት—ኤፌ. 3፡8፦*
3. *በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምድር የክርስቶስ ስዕል፣ ምልክት ነው—ዘፍ. 1፡9፤ 2 ጴጥ. 3፡5፦*
    *ሀ. በዘፍጥረት 1፡9-10 እና 13 ከሙት ውኃ ውስጥ በሦስተኛው ቀን የወጣው ምድር በሦስተኛው ቀን ከሞት ውስጥ የወጣውን ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ምሳሌ ነው።*
    *ለ. በዘፍጥረት 1፡11-12 እና 24-25 ብዙ የተለያዩ የሕይወት አይነቶች ከምድሩ ወጥተዋል፤ ይህ የሚያመለክተው ክርስቶስ የሕይወት አይነቶች ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ነው።*
    *ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ውጥን ክርስቶስ ለእኛ ምድራችን መሆን እንዳለበት ነው—ዘዳ. 8፡7-10።*
4. *ክርስቶስ እንደ መልካሚቱ ምድር፣ ከሙት ውኃ ውስጥ እንደ ወጣው ምድር በከነዓን ምድር ተገልጧል—ዘፍ. 1፡9፤ ኢያ. 1፡13።*

*ለ. በአሉታዊ ጎኑ፣ ከነዓን የሰይጣንን የጨለማ መንግሥት የአየሩን ክፍል፣ ሰማያዊውን ክፍል፣ በሰይጣን ኃይላት የተሞሉትን ሰማያት ያመለክታል—ኤፌ. 2፡2፤ 6፡12፦*

1. *ሰይጣን የራሱ ሥልጣን እና ከበታቹ ያሉ የዚህ የጨለማ ዓለም አለቆች፣ ኃይላት እና ሥልጣናት የሆኑ መላእክት አሉት—ሐዋ. 26፡18፤ ማቴ. 12፡26፤ 25፡41፤ ኤፌ. 6፡12፤ ቆላ. 1፡13።*
2. *ሰይጣን፣ የእግዚአብሔር ጠላት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስን እንደ መልካሚቱ ምድር እንዳይደሰቱት ለማስጓጎል የተቻለውን ያህል ሲያደርግ ነበር፤ እስከዚህ ቀን ድረስ ክፉ ኃይላት የክርስቶስን ሁሉን-አካታችነት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እየጋረዱ ነው—2፡8፣ 18፤ 2 ቆሮ. 4፡3-4።*
3. *የኤፌሶን መጽሐፍ በሰማያት የተለያዩ ድርቦች እንዳሉ ይጠቁማል—1፡3፣ 2፡2፤ 6፡12፦*
    *ሀ. ክርስቶስ እንደ መልካሚቱ ምድራችን ሁሉ ነገራችን ለመሆን በከፍተኛው ድርብ፣ በሦስተኛው ሰማይ ውስጥ ነው—ዘዳ. 8፡7-10።*
    *ለ. ሰይጣን በአየሩ ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ በምድር ላይ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይገናኙ እና ክርስቶስን እንዳይቀበሉ የሚያስተጓጉልበት የሰማያት የታችኛው ድርብ—አየሩ አለ፤ ይህ እስራኤልን ወደ መልካሚቱ ምድር ከመግባት ሲያስተጓጉሉ በነበሩት በከነዓናውያን ተመስሏል—ኤፌ. 2፡2።*
4. *ከነዓናውያን የወደቁትን መላእክት፣ ሰይጣንን የተከተሉትን አመፀኛ መላእክትን ያመለክታሉ፣ እነርሱም በሰይጣን መንግሥት ውስጥ ያሉ ኃይላት፣ ገዢዎች እና ሥልጣናት፣ በሰማያት ውስጥ ያሉ የክፋት መንፈሳዊያን ኃይላት ናቸው—ራእ. 12፡4፣ 7፤ ኤፌ. 6፡12።*

*ሐ. በምሳሌ የተመለከቱት የከነዓን ትርጉም ሁለት ገጽታዎች በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ ተነግሮአል፣ በዚህ ረገድ በብሉይ ኪዳን ያለው የኢያሱ መጽሐፍ ከኤፌሶን ጋር የሚነጻጸር ነው ምክንያቱም ሁለቱም መጽሐፍት የ "ከነዓን" ዘገባ ናቸው፦*

1. የእስራኤል ልጆች ከነዓን እንደገቡ፣ የክርስቶስን ብልጥግናዎች ተደሰቱ፣ በውጊያ ውስጥም ተሳተፉ—ኢያ. 5፡12፤ 6፡1-21።
2. ኤፌሶን 3፡8 ስለ ክርስቶስ ብልጥግናዎች ይናገራል፣ 1፡3፤ 2፡6፤ እና 6፡12 ስለ ሰማያት ይናገራል፤ ይህ የሚያመለክተው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስን ብልጥግናዎች መደሰት እና በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ መሳተፍ እንደሚገባን ነው።
3. ያለ መጽሐፈ ኢያሱ በኤፌሶን 6፡10-20 ያለውን መንፈሳዊ ውጊያ በሙላት ልንረዳው አንችልም።

**V. ለእግዚአብሔር አላማ መፈጸም መልካሚቱን ምድር የራሳችን ለማድረግ ከፈለግን፣ ሰይጣናዊ ኃይላትን ለማሸነፍ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ መሳተፍ አለብን—ኢያ. 6፡21፦**

ሀ. የመንፈሳዊ ውጊያን—በሰይጣን መንግሥት እና በእግዚአብሔር መንግሥት መካከል ያለውን ውጊያ—አስፈላጊነት መገንዘብ ያስፈልገናል—ማቴ. 6፡10፤ 7፡21፤ 12፡26፣ 28፤ ኢሳ. 14፡12-14።

ለ. እስራኤል የከነዓንን ምድር የራሱ ለማድረግ ዝግጁ በነበረ ጊዜ፣ ምድሪቱ በኢጋንንት-በተያዙ ሰዎች፣ በጣዖት አምላኪዎች እና በኔፊሊም ተሞልታ ነበር—ዘኍ. 13፡33።

ሐ. የወደቁ መላእክት እና የወደቀው ሰው ድብልቅ የሆኑት ኔፊሊሞች በምድሩ ላይ ይኖሩ ስለ ነበር፣ የሰው ዘር መጥራት ይችል ዘንድ እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆች ምድሩን እንዲቆጣጠሩ እና በዚያ ያለን እያንዳንዱን ሕያው ፍጥረት እንዲያጠፉ አዘዛቸው—ዘዳ. 7፡1-2፦

1. በመለኮታዊው ሃሳብ መሠረት፣ በከነዓን ምድር የነበሩት አሕዛብ ዲያቢሎሳዊ እና ከኢጋንንት ጋር የተዋሐዱ ስለነበሩ ፈጽመው መጥፋት ነበረባቸው—ቁ. 2፤ ኢያ. 11፡21-22፤ 14፡6-14።
2. ከነዓናውያን የሚያመለክቱት የወደቁትን መላእክት ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን ከክፉ መናፍስት፣ በአየር ውስጥ ካለው ሰይጣናዊ የጨለማ ኃይል ጋር ያጋጠሙትን ሰዎች ጭምር ነው—2፡2፤ 6፡12።

መ. እስራኤል ከምድሪቱ ነዋሪዎች ጋር መዋጋቱ በምድር ላይ እየተካሄደ ካለው ከሚታየው ትእይንት በስተጀርባ የማይታየውን መንፈሳዊ ውጊያ በስእል ያሳያል—ዳን. 10፡10-21፤ ኤፌ. 6፡10-20፦

1. ከበስተጀርባ መንፈሳዊ መጋደል፣ በሰው ዓይኖች የማይታይ መጋደል እየተካሄደ እንዳለ ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው።
2. በምድር ላይ ካለው ውጊያ በተጨማሪ፣ በእግዚአብሔር እና በአየሩ ላይ ባሉ ሰይጣናዊ ኃይላት መካከል ውጊያ አለ።

ሠ. የእስራኤል ልጆች መልካሚቱን ምድር የራሳቸው ያደርጉ እና ይደሰቱ ዘንድ ከከነዓናውያን ጋር መዋጋታቸው ቅዱሳን ክርስቶስን ሁሉን-እንዳካተተው ምድር ይደሰቱት ዘንድ ብልቶችን ሁሉ ጨምሮ መላዋ ቤተ ክርስቲያን “በሰማያዊ ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር” (ቁ. 12) የምታደርገውን መንፈሳዊ ውጊያ በምሳሌ ያሳያል።

ረ. ክርስቶስ መልካሚቱ ምድራችን ነው፣ እግዚአብሔር ክርስቶስን እንድናተርፍ ይፈልጋል፣ ነገር ግን በእኛና በመልካሚቱ ምድር መካከል የዲያቢሎሳዊ፣ የኢጋንንታዊ ኃይላት ንብር አለ፤ ለድሰታችን መልካሚቱን ምድር የራሳችን ለማድረግ ከፈለግን፣ እነዚህን ሰይጣናዊ ኃይላት ማሸነፍ አለብን—ቆላ. 1፡12-13፤ 2፡15፤ ኤፌ. 3፡18፤ 6፡11-12፦

1. የግድ ልንሳተፍበት የሚገባን እጅግ እውን የሆነ መንፈሳዊ ውጊያ አለ፤ የክርስቶስ አካል፣ አዲሱ ሰው እና የእግዚአብሔር መንግሥት ለሆነችው ለቤተ ክርስቲያን መገንባት ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስን ለማትረፍ ውጊያውን መዋጋት አለብን—ቁ. 10-12፤ 1 ጢሞ. 6፡12፤ 2 ጢሞ. 2፡3-4፤ ቆላ. 1፡13፣ 18፤ 2፡19፤ 3፡10-11።
2. ለድሰታችን ክርስቶስን የራሳችን ለማድረግ ከፈለግን፣ ሰይጣናዊ ኃይላትን የምንዋጋ እና የምናሸንፍ ብዙዎች የተካተቱበት ተዋጊ፣ የክርስቶስ አካል የሆነች ቤተ ክርስቲያን መሆን አለብን፣ ይህም ክርስቶስ ምድርን የራሱ ለማድረግ ተመልሶ መምጣት ይችል ዘንድ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመመሥረት እና በማሰራጨት ለክርስቶስ አካል መገንባት ክርስቶስን በይበልጥ ማትረፍ እንችል ዘንድ ነው—ኤፌ. 3፡8፤ 4፡16፤ ማቴ. 24፡14፤ ራእ. 11፡15።

**VI. በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ለመሳተፍ፣ ክርስቶስን እንደ የያሕዌ ሠራዊት አለቃ የሚገልጠውን ራእይ ማየት ያስፈልገናል—ኢያ. 5፡13-14፦**

ሀ. ኢያሱ የያሕዌ ሠራዊት የሚታየው አለቃ የነበረ ሲሆን፣ ክርስቶስ ደግሞ የከነዓንን ሰባቱን ነገዶች ለእስራኤል ለመዋጋት የማይታየው አለቃ ነበር—ቁ. 14።

ለ. የያሕዌ ሠራዊት አለቃ ከሆነው ከክርስቶስ ራእይ የተነሣ፣ ኢያሱ ሁልጊዜም በመቀደስ (በቅድስና) መቆሚያ ላይ መቆም ያስፈልገው ነበር—ቁ. 15፦

1. ቅድስና ቅዱስ የመሆን ባህሪ እና ጥራት  ነው—ሮሜ. 1፡2።
2. (ለእግዚአብሔር) መቀደስ በመቀደስ የሚመጣ ተግባራዊ ውጤት፣ በተግባር የሚገለጥ ባህሪ እና ከፍተኛ--ምርጡ የመጨረሻ ሁኔታ ነው—6፡19፣ 22።

**VII. የእስራኤል ልጆች በመጀመሪያው ውጊያቸው ድል አድራጊዎች እንዲሆኑ ያስቻላቸውን በጣም አስፈላጊ መንሥኤ ማወቅ ያስፈልገናል—ኢያ. 6፡1-20፡-**

ሀ. ወደ እርስዋ የሚገባና ከእርስዋ የሚወጣ እንዳይኖር የኢያሪኮ ፈጽማ መዘጋት የሚያመለክተው የጨለማ ኃይላት፣ በሰማያት ውስጥ ያሉት የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት መታሰራቸውን ነው—ማቴ. 12፡29፤ ኤፌ. 6፡12።

ለ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ኢያሪኮን ለማጥፋት ምንም ማድረግ አላስፈለጋቸውም ነበር።

ሐ. በእግዚአብሔር ማመን እና መታመን፣ ከእስራኤል ሠራዊት አለቃ የሚመጣውን መመሪያ ማድመጥ እና ታቦቱን በመሸከም ክርስቶስን ከፍ ከፍ ማድረግ ብቻ ያስፈልጋቸው ነበር—ኢያ. 6፡3-11።

መ. እዚህ ጋር ካህናቱ ታቦቱን መሸከማቸው የሚያሳየው በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የመጀመሪያው ማድረግ ያለብን ነገር በነገሮች ሁሉ ለእርሱ የመጀመሪውን ስፍራ፣ ፊተኛውን ስፍራ በመስጠት ክርስቶስን ከፍ ከፍ ማድረግ እንዳለብን ነው—ቁ. 4፣ 7-11፤ ቆላ. 1፡18፡-

1. የእስራኤል ሕዝብ ኢያሪኮን ባጠቁ ጊዜ፣ ይህን ያደረጉት በታቦቱ በተመሰለው ክርስቶስ አመራር ሥር ነበር—ኢያ. 5፡14፤ 6፡3-11።
2. ዋና የጦር አዛዣቸው የነበረው የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ታቦቱ ጠላቶቹን ለማጥቃት ቅድሚያውን ወሰደ—ቁ. 4።

ሠ. የመጮህ ትእዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ዝም ማለት ማንኛውንም አይነት ሃሳብ፣ አመለካከት ወይም ስሜት ባለመግለጥ ጉዳዩን በጌታ መንገድ ማከናወን ማለት ነው—ቁ. 10።

ረ. ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ በነበረው እስራኤል በኢያሪኮ ላይ በነበረው የመጀመሪያ ውጊያ ድሉ የተገኘው በእስራኤል መዋጋት ሳይሆን መለከቱን በመንፋታቸው እና በመጮኻቸው ነበር፣ ይህ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር የትእዛዝ ቃል ባለ እምነት በኩል ከክርስቶስ (ታቦቱ) ጋር የእግዚአብሔርን መመስከር እና መታወጅ ነው—ቁ. 2-5።

**VIII. ልዩና-ብቸኛው መርህ መንፈሳዊ ድል በውጊያ ላይ አለመመርኮዙ ነው—የሚመረኮዘው በውዳሴ ላይ ነው—2 ዜና. 20፡20-22፡-**

ሀ. በውዳሴአችን ሰይጣንን ድል-መንሣትን መማር አለብን።

ለ. እግዚአብሔርን የሚያወድስ ሰው ከሁሉ ነገር በላይ ከፍ ይላል፣ በውዳሴውም ያለማቋረጥ ድል-ይነሣል፤ ይህ መርህ ነው፣ ይህ ሃቅ ነው—ዕብ. 11፡30፣ 33-34፤ 13፡15።

© 2021 Living Stream Ministry